# እኔ ግን ተቀንሻለሁ!!!

"ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኘነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ!!!" አዙሪት ሆኖብናል እንደ አለመታደል ሆነና። የጥንት ባንዳዎች ትንሽ ይሉውኘታ ነበራቸ እንደ አይጥ ተደብቀው ነብር የሚኖሩትና ተጠቃሚ የሚሆኑት። አሁን ግን በአደባባይ ጀግኖች ነን ሲሉ በፍጹም ይልውኘታ ቢስነት መሆኑ እጅግ ኢትዮጵያዊነት ባህል መውደቁን ያየንበት ጊዜ ቢኖር ከ1983 ዓ.ም በኋላ ነው።ፍጹም ባንዳዎች በጀግንነት የሚታወቁባት ሀገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ ናት።

የዶር/ አብይ መንግስት "በኢትዮጵያ ያሉትን የቀን ጅቦችን ሲያወግዙ ለምን በዋሽንግተን ያሉትን የቀን ጅቦች የትግላቸው ፊታውራሪ ማድረግ ፈሉጉ?" ይህ ለምን ይሆን ዶ/ር አብይ? በኢትዮጵያ ትግል ፊት አውራሪ ለመሆን መለኪያው የሲ.አይ.ኤ ተላላኪ መሆን ግዴታ ይሆን? የመደመሩ ፊት አውራሪነት መለኪያው ይህ ከሆነ " ፈጣን ነው ባቡሩ ፈጣን ነው ባቡሩ ፈጣን ያልሆናችሁ እንዳትሳፈሩ" ከሆነ ወራጅ አለ ጠቅላይ እዬ።

እስኪ ጠቅላይ እዬ ልጠይቅዎት? አንድን ግለሰብ ጠርቶ ዳጋግሜ ብደውልለት ለስልኬ መልስ ስላሰጠኝ እከሌ ነገርልኝ ተቀይሜዋለሁ ሲሉ አድምጫለሁ። እንደው ልጠይቆት አንዱን የቀን ጅብ አውግዞ ሌላውን የቀን ጅብ ማቆላመጥ ከአንድ መሪ ይጠበቃል? እንዴህ ከሆነማ ወራጅ አለ።

ጠቅላይ እዬ ትላንተ አህዛቡ የትግሬዎች መንግስት/ ህ.ወ.ሃ.ት/ ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር ፊት አውራሪ የነበሩና የኢትዮጵያ ህዝብ የበደሉ ሰዎችን ዛሬም ፊት አውራሬ ማድረግ እውነት ይህች ሴራ የእርስዎ ወይስ የሲ.አይ.ኤ? ይመልሱልኝ እውነተናኛ ክርስቲያን ከሆኑ? ሌሎቹስ ኦሮሞ ፈርስት ይሉ የነበሩት የማን ተላላኪ ናቸው?

ኤርትራ ሸምቀው ምንም ሳይሰሩ የዲያስፎራውን ገንዘቡን ሲዘርፉት፣ሲያላግጡበትና ሲያርዱ የነበሩ የቀን ጅቦች የምዕራባዊያን ተላላኪ በመሆናቸው ብቻ ፊት አውራሪ ሆነው እንደለመዱት ከች ማለታቸው እጅግ አሳዛኝና አስደንጋጭ ሆኖብኛል? እኔ ነጻ የሆነች ኢትዮጵያን እንጂ ወራዳውን ኢትዮጵያ ለማየት የማልፈልግ ዜጋ በመሆኔ ተቀንሻለሁ!!! ወራጅ አለ ነው መልዕክቴ።

እጅግ ያሳዘነኝ ትላንት የዘረፉት ሳይበቃቸው የስታር ባክስ የቀን ጅቦች ዛሬም ገንዘብ ለማሰባሰብ ፊት አውራሪዎች ለመሆን እራሳቸውን መርጠዋል።የቀን ጅብ ማላት የህዝብ ገንዘብ የዘረፉትን ኢትዮጵያንና ትውልደ ኢትዮጵያንን በጋር የሚመለከት መስሎኝ ነበር? ነገርግን ውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊያንን መዝረፍ የቀን ጅብ አያስብልም፤እኔ ግን ሁሉንም የሚያካትት መስሎኝ ነብር።ጠቅላይ እዬ ይቅር ይበሉኝ እኔ ወራጅ ነኝ።

በእውነት ሰው ስንት ጊዜ ይታለላል? በቅንጅት ጊዜ አታለሉን፣ቃሊቲ እስር ቤት አታለሉን፣ኤርትራ በርሃ ገባን ብለው አታለሉን፣አሁን ደግሞ ከጠቅላይ እዬ ጋር ሆነው ሌላ ትያትር እየሰሩብን ነው።በሬ ከአራጁ ጋር እስከመቼ? እንስሳ እንኳን ሁል ጊዜ አይታለልም። ቅዱስ መጽሐፍ "እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱ መጠን እግዚአብሔር ለማይረባ/ለማያስተውል አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው" ይላል። እግዚአብሔርን አለማውቃችን መመኪያችን ሰዎች ሆነዋል፤ ቅዱስ ምጽሐፍም በዚህ ላይ የሚለው አለ። "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦በሰው የሚተማመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ልቡንም ከእግዚአብሔር የሚመልስ ሰው እርጉም ነው።"ይላል። እኛ ዛሬ አሜሪካ ምን አለች ሆኗል።እምዬ ሚኒልክ የጊዮርጊስን ታቦት ይዘው መዝመታቸው እግዚአብሔርን የያዘ እንድምያይወድቅ ሙሉ እምነት ስለንበራቸው ነበር።

አንድ የኤርትራ ትውስታዬን ላጫውታችሁ እኔ ኤርትራ እውነተኛ ትግል አለ ብዬ ገብቼ ነብር፤በሰዓቱ አቶ አንዳርጋቸው ከአቶ ኢሳያስ ጋር አንድ ቀን ከተገናኙ በኋላ ኢሳያስ በቀጠሮ በቀጠሮ ስላሰለቸ አቶ አንዳርጋቸው ምርር አንዳለው አንድ ቀን አጫወትኝ።በሰዓቱ ለትግሉ ይመስለኝ ነብር።ትግሉን በተመለከት መነጋገር የነበረበት ይህንን ከሚመለከታቸው ክፍል እንጂ ከአቶ ኢሳያስ ጋር አለመሆኑን በኋላ በሹክሹክታ በኋላ የስማሁት ነገር ነበረኝ።አሁን ግን አቶ አንዳርጋቸው ታፍኖ ሲወሰድና ዶ/ር ብርሃኑ ሲገባ ለምን ትግል በሌለበት ገባ ብዬ ግራ ሲገባኝ ነብር።ጉዳዩ ሸንጉር መሆኑን ዶ/ር አብይ ከኢሳያስ ጋር እንዴት በአንዴ ተስማሙ ብዬ ሳስብ ለካ ነገሩ ወዲህ ነው።ዶ/ር ብርሃኑ ከጌቶቹ ከሲ.አይ.ኤ ተልኮ ተስጥቶት መሆኑ አሁን ግልጽ ሆነልኝ።አቶ አንዳርጋቸው ነገሮቹን በተቀላጠፈ ሁኔታ ባለመፈጸሙ ይሉኝታ ቢሱና ምላጩን ዶ/ር ብርሃኑን ለመላክ አንዳርጋቸው እንዲታፈን ተደረገ።ይህን ጨዋታ በመጫውቱም ድርጅቱና ብርሃኑ ጠቅላይ እዬ ፊት አውራሪ አደረጓቸው።

ጠቅላይ እዬም ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በንግርት ያምናል ብለው " እናቴ ከመሞቷ በፊት ሰባተኛው/7ኛው/ ንጉስ" ትሆናለህ ብላኝ ነብር ይሉናል፤እናታቸው ጠንቋይ ወይስ የዘጉ መለኩሴ ነበሩ?ይህን ቢመልሱልኝ እጅግ ደስ ይለኛል። እንዲህ አይነቷን ሺወዳ ታናሽ ወንድሜ ነፍሱን ያማረውና Poor psychology ተወት አድርገው ወደ ስልጥን እንዲመጡ የረዳዎትን የውጭ አካል ቢነግሩን እኛም የግዳችን እንከተሎት ነብር።እናም ይህቺን poor psychology ነቂ ስለሆንባት

እባክዎን ሌላ መሸውጃ ያምጡልን።ምክንያቱም እኛ ኢትዮጵያዊያንን ለመታለልና ለማጨብጨብ አስቸጋሪዎች ስላልሆንን አይስጉ።

ሌላው ደግሞ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ማለት መንግስቱም ኃይለማሪያምም "ኢትዮጵያ ትቅደም ለማለት ማንም አልቀደመውም።እርሶም ኢትዮጵያ በማለቶ ብቻ እንምኖትና የሽግግር መንግስት አያስፈልግም እንበሎት። እኔ ታማኝ አይደለሁም ለድራማ ሥራ አልተፈጠርኩም።እስኪ ቪድዮውን ይዩት አነጋገሩ ከልቡ የመነጨ እንዳልሆኑ በግልጽ ይታይበታል።ከጀርባው ምን አለ እግዚአብሔር ይወቀው።

ጠቅላይ እዩ ትላንት ኤርትራ ውስጥ በስውር እስር ቤት ተሰውረው ያሉ ውድ ኢትዮጵያዊያን መኮንኖችና ወታደሮች ይለቀቁ ሲሉ የነበሩት ቲያትረኛ ዛሬ ደግሞ ይህን ትተው የኢትዮጵያ ወታደሮ ጡረታቸው ይከበር ሲሉ ሰምቻለሁ።እኔ ይህም ከተደረገ ልክ እንደ አንድ ቅን ኢትዮጵያዊ ያስደስተኛል።"ነገርግን ውሸን የበላ ውሾ ይሁን" የምትለውን ሽወዳ ስለማልወዳት ነው። በጽሁፌ ላይ የቀድሞ የኢትዮጵያ ወታደሮች የሚለው ቃል ስለሚቀፈኝ ነው።ለእኔ እስከአሁንም የኢትዮጵያ ወታደሮች ናቸው። የወያኔ ሰራዊት ቅጥር ነፍሰ ገዳዮች/ Mercenary/ እንጂ ምንም መለኪያ የገዛ ወገኑን የሚገል ኢትዮጵያዊ ጦር ሊባል አይችልም ። ስለዚህም ነው የሽግግር ምንግስት ወታደር መኖር ይገባል የምለው። ጠቅላይ እዩም ሽግግር የሚለውን ቃል የሚጠሉት በሦስት ነገሮች ይመስላኛል ሀ.ነጻ ፍርድ ቤት ለ.ነጻ ምርጫ ቦርድ ሐ.ነጻ የኢትዮጵያ ጦር ስለማይፈልጉ!!!እኔህ ከሌሉ ወራጅ አለ እኔ ግን ተቅንሻለሁ።

እስስት መልኳን እንደምትለውጥ ጠባያቸውን እንደዚሁ እንደሚለውጡ ሙደኞች ጋር በፈጣኑ ባቡር መሳፈር ስለማልችል ወራጅ አለ የምለው። እነዚ ፈጣኖች አንድ ወቅት የኦነግ ባለስልጣኖች ለፍርድ ይቅረቡ ብለው ከፍተኛ ቅስቀሳ ጀምረው ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እጥፍጥፍ ብለው ከዚህ ከኦነግ ባንዲራ ፊት ለፊት ተቀምጬ እናገራለሁ ብዩ አስቤም አልሜም አላውቅም ብለው ሲናገሩ በማየቴና በመስማቴ እጅግ አዝኜ ነበር ለካ ስኳር የሰውን ልጅ አዕምሮ ለማንከረባበት ቁልፍ ሚና እንዳለው ባለማወቄ ነበር። ለሁሉም እግዚአብሔር ልቦና ይስጣቸው።

መደመር ማለት ከሚቀንሱት ጋር ሳይሆን ከሚደምሩት ጋር መደመር መስሎኝ ነበር፤ነገሩ አሁን እንደገባኝ ከሚቀንሱት ጋር መሆኑን አሁን ተርዳሁ።

ውድ ኢትዮጵያዊያን "እንደ ወሎ ፈረስ እራሳችንን ለጉመን ዉኃ በቀደዱለት ቦይ እንሚፈስ አንፍሰስ ሰክነን እንጓዝ።

እስኪ ተጠየቁ ?

1ኛ ዶ/ር ካሳ ከበደ ለምን ወደ ኢትዮጵያ በጠቅላይ እዩ ተጠሩ? ለምንስ ሄዱ?

2ኛ.ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና አቶ አንዳርጋቸው በጠቅላይ እዩ በጣም ተፈላጊ ሆኑ? 1983 ዓ.ም ፊት አውራሪ አሁንም ፊት አውራሪ እንዲሆኑ ለምን ተፈለገ?እኒህ ሰዎች ኢትዮጵያን ለመበተን ከተሰፋዩ ገ/አብ ጋር የነበራቸው ዝምድና ምን ያህል እንደሆነ እየታወቀ ኢትዮጵያን ለማዳን ፊት አውራሪ ሆኑ? ኤርትራ ትግል ያለ መስሎኝ ለትግል ገብቸ በነበረበት ጊዜ አቶ አድራርጋቸአው "የደራሲውን ማስታወሻ" ረቂቅ ሲያነብልኝ ለምንድን ነው ለዚህ ሰው መጽሐፍ ከማርቀቅም በላይ የምታትሙለት "የቡርቃን ዝምታ" ጽፎ ወገንን ያፋጀ ሰው እኮ ነው ስለው አቶ አንዳርጋቸው የመለሰልኝ የቡርቃ ዝምታ ምን ችግር አለው ነበር። ይህንን ሲለኝ አቶ ፈንታሁን አየነው አሁን ካልጋሪ/ካናዳ/ ያለ የትግል ጓዴ ምስክሬ ነው። አቶ አንዳርጋቸ ለማስተባበል ፍላጎት ካላው ለመከራከር በማንኛውም ጊዜ ዝግጁ ነኝ።ሌላው ደግሞ ፕሮፌሰር አስራትን ዳግም መግደል ነውና ከነዚ ሰዎች መደመር ስለማልፈልግ ወራጅ አለ ብያለሁ።ይቅርታ መባባል እሰዮ ነገርግን እኔህ ሰዎች ይቅርታ ጠይቀዋል ወይ? ለመጠየቅስ ወኔ አጥተው ወይስ ወንጀለኛ አይደለንም ለማለት።ኤርትራ ለትግል ገብተው የሞቱትስ ወገኖቻችን አያሳዝኑም?እኒህ ሰዎች ተጠያቂ አይደሉም ማለት በወገን ላይ መቀለድ አይሆንም?

ኢትዮጵያን ለመበተን የተሰልፉ ህ.ወ.ሃ.ት ብቻ ነው ብሎ ማሰብ እጅግ ጅልነት ነው፤ዋሽንግተን ያለው ሁለተኛ የቀን ጅብ ትልቅ ሚና እንደነበረው የማይረዳ ብዙ በደነፍስ የሚነጉድ በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ መኖሩን ማስተባበል የጅል ጅልነት ነው።በውጭ የሚኖረ ዲያስፎራ እና የአህዛቡ ወያኔ ተውካዮች ምክር አባላት የሚለዩት አንዱ ቡድን ኢትዮጵያ መኖሩ ሁለተኛው ቡድን ውጭ መኖሩ እንጂ ጭብጨባ ሲሰማ ለማጨብጨብ የተፈጥረ አጨብጫቢ ነው። በአንድ ወቅት መምህር ግርማ አንድ የመንፈስ ችግር ያለበትን ሲያስለፈልፉት የተናገረው ነገር "ይህን አጨብጫቢ ሕዝብ ተውት ሲወደሰም ሲረገምም የሚያጨበጭብ ነው!!!" ያለው እንደቀልድ ነበር ያየሁት፤ዛሬ ግን በተጨባጭ አየሁት።"እስኪ ቪድዮውን እዩት የሽግግር መንግስት አያስፈልግም ሲባል የሚያጨበጭብ በእውነት ጤነኛ ሰው ነው?" የኢትዮጵያን ፖለቲካ ተንታኞች ነን የሚሉትን እነ ጂጅን ማየት በቂ ነው። በዚህ ዘመን ቁልፍ ሚና ያላቸው የዲያስፎራው የቀን ጅቦችና በደመነፍስ የሚንቀሳሱት "ጥራዝ ነጠቅ ፖለቲከኞች" እንጂ የተማረው፣በሳሉ ፖለቲከኛና ሀገር ወዳዱ አታውቅም ተብሎ አድማጭ አጥቶ ተሸማቆ መቀመጡ ከማንም የሚሰውር አይደለም።

ለምሳሌ፡

ሀ .ኢ.ህ.አ.ፓ ከአረመኔው የደርግ መንግስትና ከአህዛቡ የትግሬዎች መንግስት/ህ.ወ.ሃ.ት/ እንዲሁም ከሻቢያ ጋር በመፋለም ለምን ብዙ ጓዶቹን ማጣት አስፈለገው? ለሲ.አይ.ኤ አሽከር ቢሆን ኖሮ በሰዓቱ በትግራይ ሳይቀር ተቀባይነት ስለነበረው በዘመኑ ብዙ ጦር ስላለው ሥልጣን ለመያዝ እጅግ ለኢ.ህ.አ.ፓ ቀላል ነበር።አንድ ማሳያ ልንገራችሁ ለገሰ አስፋውን የፈታ አህዛቡ የትግሬዎች መንግስት ለምን ያፈናቸውን የኢ.ህ.አ.ፓ አባላትን እስከዛሬ አልፈታም?

ዶ/ር ብርሃኑ ቃሊቲ ከዞን አንድ ዞን አምስት ተቀይሮ መጽሐፍ ሲጽፍ ኢ.ህ.አ.ፓን ጩካኝ አድርጎ ለመጻፍ ለምን ፈለገ? በአንድ ወቅት ፕሮፌሰር መስፍን ስለዚህ መጽሐፍ ተጠይቀው የሰጡት መልስ “ብርሃኑ ለብርሃኑ የጻፈው ነው” ማለታቸው መጽሐፉ የጻፈው ለራሱ እና ለኢትዮጵያ ጠላቶች ጥቅም ሲል መሆኑን ልብ ያለው ልብ ይበል። ልብ የሌለውም ያ ያ ጅቦና ውሾን ተረት ያደምጥ። ይህን ስል የኢ.ህ.አ.ፓ አባል እንዳልሆንኩ እንዲታወቅልኝ።

ለ.የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መስራችና ሊ/መንበር ኦባንግ ሜቶን የሚያከል ኢትዮጵያው በጠቅላይ እዬ መጀመሪያ ስማቸውን መጥራት ለምን ተዘነጋ? እውነተኛ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው ሲ.አይ.ኤ አልውደዳቸውም።ቢያንስ ቢያንስ በአንድ ወቅት ፋሽስቶች በመኪናቸው ጨፍልቀው ሊያጠፏቸው ሲሉ የኢትዮጵያ አምላክ በጥበቡ ያተረፋቸውን ውዱና የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጅ እንዴትሊረሱ ይገባቸዋል? ይህ የዕቃ ዕቃ ጫወታ መቸ ይሆን የሚያበቃው?

ተደመር ተደመር ተደመር ይሉኛል፣

ከእንግዴ ልጅ ጋራ መደመር መሮኛል ።

ወራጅ አለ ወራጅ ወራጅ

“የኢትዮጵያ አምላክ ኢትዮጵያን ይጠብቃት” አሜን! አሜን!አሜን!

አንተነህ ጌትነት/ የሶማው ሺፊ/ ከባእድ ሀገር ሜልበርን አውስትራሊያ

ትችታችሁ ከልቤ እፈልጋለሁ በዚህ ኢሜል ጻፉልኝ muluadamche@gmail.com